በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ


# የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት

## የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ዘርፍ

### ለልዩ የፍላጎት/አካቶ ትምህርት ሜይንስትሪሚንግ ማኑዋል ዝግጅት ለውይይት የቀረበ መነሻ ሠነድ

[redacted]

▪


FOR A FAIR SELECTION EVERYBODY HAS TO TAKE THE SAME EXAM: PLEASE CLIMB THAT TREE

# የማንዋሉ ይዘት

- መግቢያ
- አስፈላጊነት
- አላማ
- የቃላት ፍቺና የፅንስ-ሃሳቦች መግለጫ
- የአካቶ ትምህርት ስርዓት አስፈላጊነትና የትግበራ መርህ
- በክልሉ ት/ቢሮ ስር የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶችና የስራ ክፍሎች በልዩ ፍላጎት/ በአካቶ ትምህርት ትግበራ የሚጠበቅባቸው ሚና

## መግቢያ

- የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ሁሉም ዜጎች ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መብት እንዳላቸው ከማረጋገጡም ባሻገር ተገልለው ለኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ የሀብትና የሙያ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ይደነግጋል፤

- በተለይም የህገ መንግስቱ አንቀፅ 41 መንግስት የተሃድሶና የድጋፍ አገልግሎቶችን ለአካል ጉዳተኞች የመስጠት ሃላፊነት እንዳለበት ይገልፃል፤ ከዚህም በተጨማሪ ከአካቶ ትምህርት ጋር አግባብነት ያላቸውን ልዩ ልዩ ዓለም ዐቀፍ ድንጋጌዎች፤ ኮንቬንሽኖችና ደንቦች አፅድቋል።

# የቀጠለ.....

- በተለይም የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 24 ለአካቶ ትምህርት አፅንኦት የሰጠውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን የ2006 (እኤአ) የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ኮንቬንሽንን ተቀብሎ በማፅደቅ የአገሪቱ ህገ መንግስት አካል እንዲሆን አድርጓል፡፡
- ፖሊሲውም መሠረት በማድረግ እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ትምህርትን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናትና የትምህርት ዕድል ላላገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ስትራተጂ በሀገር አቀፍ ደረጃ  በ2012 (እ.ኤ.አ.) በመከለስ አዘጋጅቷል፡፡

## የስትራቴጂው አጠቃላይ ግቦችም ፡-

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሁሉም ህፃናት፤ ወጣቶችና ጎልማሶች የትምህርት ተደራሽነትን እንዲያገኙ ማድረግ፣
- አካል ጉዳተኛ ህፃናት በአካቶ ትምህርት ስርዓት የመማር መብት እንዳላቸው የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማዳበር፣
- አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተካተው የሚማሩበትን መንገድ ለማመቻቸት ስርዓተ ትምህርቱ አሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መሻት፣
- የመምህራንን አቅም በስልጠና ማጎልበት
- የድጋፍ መስጫ ማዕከላትን ማስፋፋትና ማጠናከር ናቸው።

## የቀጠለ.....

- በመሆኑም የክልሉ ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀውን የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን በመተግበር ትምህርትን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናትና የትምህርት ዕድል ላላገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ በርካታ ተግባራትን ቢያከናውንም፤ ከትምህርት ገበታ ውጭ ያሉ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ቁጥር እጅግ ብዙ እንደሆነ ከክልሉ ት/ቢሮ ከትምህርት መረጃ አመራር የተገኘው መረጃ ያመለክታል።( በቅድመ መደበኛ 11.9% መጀመሪያ ደረጃ 29.1% በሁለተኛ ደረጃ 17.8 % )
- ለዚህም ምክንያት ከሚጠቀሱ በርካታ ችግሮች መካከል በክልሉ በሚገኙ ት/ቤቶች ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎችን ወደ ት/ቤት በማምጣት በት/ቤት ለማቆየት የሚከናወኑ ተግባራት በሁሉም ባለድርሻ አካላትን ዘንድ የጋራ ግንዛቤን በመፍጠር እና ቅንጅታዊ አሠራርን በመከተል የሚከናወኑ እንዳልሆነና ለተወሰኑ የስራ ክፍሎች የተተወ ተግባር መሆኑን በዋናነት ይጠቀሳል።

## የቀጠለ.......

- በመሆኑም ከትምህርት ገበታ ውጭ ያሉ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ወደ ት/ቤት ለማምጣትና በት/ቤትም ውጤታማ የቆይታ ጊዜ እንዲኖራቸው ለማስቻል በሁሉም ባለድርሻ አካላትንና የስራ ክፍሎች የጋራ ግንዛቤ በመጨበጥ የልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ትግበራን በባለቤትነት መንፈስ እንደ ዘርፈ ብዙ ጉዳይ በዕቅዳቸው በማከተት ቅንጅታዊ አሠራርን በመከትል ለመተግበር እንዲቻል ይህ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ሜይንስትሪሚንግ ማኑዋል ተዘጋጅቷል፡

## 2. የማንዋሉ አስፈላጊነት

- ከትምህርት ገበታ ውጪ የሚገኙ የተለያዩ የአካል ጉዳት ያለባቸው ህፃናት/ተማሪዎችን በተቀናጀ መልኩ ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ ለማድረግና ምቹ የትምህት ቤት ሁኔታ አካባቢን በመፍጠር በትምህርት ቤት በማቆየት የተሻለ የትምህርት ውጤት እንዲያስመዘግቡ እንዲችሉ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ትግበራን እንደ ዘርፈ ብዙ ጉዳይ የተለያዩ የስራ ክልሎች የዕቅዳቸው አካል አድረገው እንዲተገብሩ ለማድረግ ......

# 3. የማንዋሉ ዓላማ

## 3.1. የማንዋሉ አጠቃላይ ዓላማ

- የተለያዩ የስራ ክልሎች የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ትግበራን የዕቅዳቸው አካል አድረገው እንዲተገብሩ በማድረግ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎና ተደራሽነትን ለማሳደግ ነው፡፡

## 3.2. የማንዋሉ ዝርዝር ዓላማዎች ፡-

- በባለድርሻ አካላትንና በተለያዩ የሥራ ክፍሎች መካከል በአካቶ/ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ትግበራ እና ፅንሰ-ሃሳብ ዙሪያ የጠራ የጋራ ግንዛቤ በመጨበጥ እንዲተገብሩ ለማድረግ
- በባለድርሻ አካላትንና እንዲሁም በት/መምሪያዎች በት/ፅ/ቤቶች በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ዕቅድ ውስጥ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳይን በማካተት እንዲተገብሩ ለማድረግ

# የቀጠለ.....

- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳይን እንደ ዘርፈ ብዙ ጉዳይ በመገንዘብ ለመትግበር የሚያስችል ቅንጅታዊ አሠራርን በመፍጠር ተግባሩን በውጤታማነት ለመምራት
- በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻና አስፈጻሚ አካላትን እንዲሁም በት/ቢሮው፣ በት/መምሪያዎች እና በት/ፅ/ቤቶች በተለያዩ የሥራ ክፍሎችን በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ትግበራ ዙሪያ ያላቸውን ሚና ተግባርና ሃላፊነት ለማሳወቅ

# 4. የቃላትና የፅንስ-ሃሳቦች መግለጫ

**4.1 ልዩ ትምህርት (Special Education)፡-** ልዩ ትምህርት ለአካል ጉዳተኞችና የማህበራዊና ስሜታዊ ችግሮች ወዘተ ያሉባቸው ተማሪዎች በልዩ የመማሪያ ክፍሎች፤ በዩኒቶችና በልዩ ትምህርት ቤቶች በተለየ መልኩ ለማገዝ የሚደረግ የትምህርት አደረጃጀትን ያጠቃልላል።

- የሚያስተምሩ መምህራንም እነዚህን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ለመርዳት የተለየ ስልጠና የወሰዱ መሆን ይኖርባቸዋል

**4.2 ልዩ ፍላጎት ትምህርት (Special Needs Education)**

- ልዩ ፍላጎት በመሰረቱ ልዩ ትምህርትን ተክቶ የመጣ አደረጃጀት እንጂ ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው ፅንሰ- ሃሳቦች አይደሉም። ይልቁንም፤ ለአካል ጉዳተኞችም ሆነ የማህበራዊና ስሜታዊ ችግር ያሉባቸውን ጨምሮ የመማር ችግሮች ያሉባቸውን ተማሪዎች ለማገዝ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ሁሉ ያካትታል።

# ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች (Learners with Special Educational Needs

ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የምንላቸው በተለያዩ ምክንያቶች ሳቢያ
የመማር ችግሮች የሚያጋጥማቸውንና በዚህም ሳቢያ የአጭርና የረዥም ጊዜ
ተጨማሪ ድጋፍን የሚሹ ተማሪዎችን በሙሉ የሚያጠቃልል ሲሆን፤ በሌላ
አገላለፅ እነዚህ ተማሪዎች የመማርና የዕድገት እንቅፋቶች የተጋረጡባቸው
ልጆች ናቸው።

## ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች

## 4.4 አካቶ ትምህርት (Inclusive Education)


- በዩኔስኮ (እ.ኤ.አ.2005) አገላለፅ "አካቶ ትምህርት የትምህርት ስርዓቱን በማጎልበት ትምህርትን ለሁሉም ልጆች ለማዳረስ የሚደረግ ሂደት ነው"

- አካቶ ትምህርት በድህነት፤ በስርዓተ ፆታ፤ በዘር፤ በቋንቋ ወይም በአካል ጉዳት ልዩነት ሳያደርግ ሁሉንም ተማሪዎች የማስተናገድ ዝግጁ የሆነ የትምህርት ስርዓት ነው፡፡

## 4.5 መቀላቀል (Integration)

- በአካቶ ትምህርት አቀራረብ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ድጋፍ እየተደረገላቸው ሙሉ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በመደበኛው ክፍል ውስጥ ሲሆን በመቀላቀል አቀራረብ ግን እነዚህ ተማሪዎች በመደበኛው ክፍሎች ውስጥ እንዲማሩ ለሙሉ ቀን ወይም ለግማሽ ቀን (ለተወሰነ ጊዜ) ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

# ማግለል፣ መለየት፣ ማቀላቀልና ማካተት



## 4.6. ተዘዋዋሪ /ተንቀሳቃሽ መምህር (Itinerant Teacher)

- **ተዘዋዋሪ መምህር** በልዩ ፍላጎት ትምህርት በድግሪ ደረጃ የተመረቀ ባለሙያ ሲሆን በዋናነት በልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ድጋፍ መስጫ ማዕከል የሚያገለግል ሆኖ ለሳተላይት ት/ቤቶች ፣ ለመደበኛ መምህራን ፤ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎችና ለወላጆች የምክርና የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

## 4.5 . የድጋፍ መስጫ ማዕከል (Resource Center)

- የድጋፍ መስጫ ማዕከል የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎችን ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች መገልገያ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን፤ የአካል ድጋፍ መስጫ መሳሪያዎችንና ለሁሉም ተማሪዎች የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን የያዘ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ነው፡፡

## 5. የአካቶ ትምህርት ስርዓት አስፈላጊነትና የትግበራ መርህ

- አገራችን አካል ጉዳተኞች በትምህርት ስርዓቱ በሁሉም ደረጃዎች ውስጥ ተካተው የመማር መብት እንዳላቸው ዕውቅና የሚሰጠውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የ2006 (እ.ኤ.አ.) የአካል ጉዳተኞች መብቶች ጥበቃ ኮንቬንሽንን ተቀብላ ማፅደቀ
- የተጠቃሚዎችን የኑሮ ደረጃ ከማሻሻሉም ባሻገር ሁሉም ዜጎች ለራሳቸው ክብርና ዋጋ የመስጠት ስሜትን ያዳበሩ አምራች ዜጎችን ለማፍራት ያስችላል፤
- ለግለሰቦችም ሆነ ለማህበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ያስገኛል፤

# የቀጠለ.......

- መድልዎን በማጥፋትና ማህበራዊ ዕኩልነትን በማስፋፋት ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብን ለመፍጠር አስተዋፅዖ ያበረክታል፤
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለማጠናቀቅና የትምህርት ዘላቂነት ያለው የትምህርት ልማት ግቦችን ለመምታት ይረዳል፤
- በአገሪቱ ውስጥ ልዩ ትምህርት ቤቶችን ከማቋቋም ይልቅ ወጭ ቆጣቢና አዋጭ ነው፤
- አካል ጉዳተኛ ህፃናት ከቤተሰቦቻቸው ጋር እየኖሩ እንዲማሩ ያደርጋል።

## 6. በክልሉ ት/ቢሮ ስር የሚገኙ ዳይሬክቶሬቶችና የስራ ክፍሎች በልዩ ፍላጎት/በአካቶ ትምህርት ትግበራ የሚጠበቅባቸው ሚና

### የመምህራንና የት/ት አመራር ልማት ዳይሬክቶሬት

- በአጫጭር ስልጠናዎች መምህራንን በአካቶ ትምህርት ፕሮግራም ትግበራ አቅማቸውን የማሳደግ ስራን በስፋት ማከናወን
- የምልመላው መስፈርትና ሂደት ልዩ ፍላጎት ያላቸው ምልምል ዕጩ ሰልጣኞች እንዲያማክል አድርጎ መስራት
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ለማስተማርና ለማገዝ እንዲችሉ ለመምህራን በብሬል ትምህርትና በምልክት ቋንቋ ተጨማሪ የክህሎት ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- የክላስተር ማዕከላት በሆኑ ትምህርት ቤቶች በተለያዩ ርዕሶች ለመምህራን በሚሰጡ ስልጠናዎች ዉስጥ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮችን አካቶ መስጠት
- የአካል ጉዳት ያለባቸው መምህራንን ተጨማሪ የክህሎት ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት

- የስርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ክለሳ የልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ትምህርትን ባካተተ መልኩ ማከናወን
- በስርዓተ ትምህርት ላይ የሚካሄድ ግምገማ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ጉዳዮችን ባገናዘበ መልኩ ማከናወን
- የመማሪያ ማስተማሪያ መፃህፍትን ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ባማከለ ሁኔታ አስማምቶ ማዘጋጀት
- በክልሉ ለሚገኙ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የአካል ድጋፍ መሳሪያዎችና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው የትምህርት መርጃ መሳሪዎች አቅርቦት መኖሩን በማረጋገጥ እንዲሟል ማድረግ

# የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናትን ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ለማድረግ የተለያዩ የህዝብ ንቅናቄ መድረክን መፍጠር
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናትን በትምህርት ቤት ለማቆየት ምቹ የመማር ማስተማር ሁኔታንና አካባቢን መፍጠር
- በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ልዩ ፍላጎት ላላቸው ህጻናት የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ ድጋፍ ማድረግ
- በት/ቤቶች የሚሰጡ የትምህርት ሂደትና አገልግሎቶች የአካታች መርህን እየተከተሉ እንዲያከናውኑ ማድረግ ፣መከታተል፣ መደገፍ
- የአካቶ ትምህርት ክበብን የማቋቋምና የማደራጀት ስራን በትኩረት ማከናወን
- በድጋፍ መስጫ ማዕከላት የኮር ቲም እንዲቋቋም መደገፍ፣ መከታተል
- በትምህርት ቁሳቁሶችና በድጋፍ መስጫ መሳሪያዎች የተሟሉ የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማእከላትን ማቋቋም፣ አፈፃፀሙን መከታተልና መደገፍ

# የትምህርት ቤት መሻሻል የቀጠለ..........

- በትምህርት ቁሳቁሶችና በድጋፍ መስጫ መሳሪያዎች የተሟሉ የአካቶ ትምህርት የድጋፍ መስጫ ማእከላትን ማቋቋም፣ አፈፃፀሙን መከታተልና መደገፍ
- የፖለቲካና የትምህርት አመራሩን፤ የሃይማኖት መሪዎችን፤ የአገር ሽማግሌዎችን እንዲሁም ማህበረሰቡን ባጠቃላይ በተለያዩ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮች ዙሪያ ቀጣይነት ባለው መልኩ በክልሉ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያዎች፣ ለትምህርት ተቋማት አመራሮች በልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ትግበራ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን መፍጠር ፣ አጫጭር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች መስጠት

## የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት

- ‘School NET’ን የአይ ሲ ቲ መሰረተ ልማትን በማሻሻል በሁሉም ደረጃ ማቋቋምና አይነ ስውራንንና መስማት የተሳነቸውን ተማሪዎችን ባካተተ መልኩ በኮምፒዩተር የታገዘ የብሬልና የምልክት ቋንቋ ትምህርት መስጠት
- የፕላዝማ ስርጭት መስማት ለተሳነቸው ተማሪዎች ትምህርት ከፍተኛ ድጋፍ ስለሚያደርግ ተደራሽ የሚሆንበት ስርዓትን መፍጠር
- ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚያገለግሉ አዳዲስ የትምህርት ቁሳቁሶችንና የድጋፍ መሳሪያዎችን ቴክኖሎጂን ማፈላለግና ማስተዋወቅ

## የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ዳይሬክቶሬት

- ተጨማሪና ልዩ ሙያ ላላቸው እንደ ተዘዋዋሪ መምህራን፣ የብሬል መምህራንና የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች የምዘና መሳሪያ ማዘጋጀት
- የአካል ጉዳተኛ መምህራንን ችግርን ያማከለ የምዘና ስርዓትን መዘርጋትና ልዩ ዕገዛን የሚያገኙበትን ሁኔታን መሰረት ባደረገ መልኩ ማከናወን

## የፈተና ዝግጅት አስተዳደርና የት/ምዘና ጥናት ዳይሬክቶሬት

- በክልል አቀፍና በክልል ደረጃ ለተማሪዎች የሚዘገጁ ፈተናዎች የልዩ ፍላጎት ተመሪዎችን ልዩነት ያገናዘቡ ሆነው እንዲዘጋጁ ማድረግ
- መስማት የተሳነቸውና አይነ ስውራን ተማሪዎች ውጤት አያያዝን ከሌሎቹ አቻ ጓደኞቸቻቸው በልዩነት የሚታይበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን የሚያካትት ተስማሚ ክልላዊና ክልል አቀፍ ፈተናዎችን ለማዘጋጀት ስትራቴጂ በመንደፍ መተግበር

## የመምህራንና ሠራተኞች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

- የልዩ ፍላጎት ት/ት ባለሙያዎች፣ መምህራንና ተዘዋዋሪ መምህራን ቅጥር፣ ዝውውር፣ ደረጃ ዕድገትና ጡረታ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ
- በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠኑ መምህራንን በተዘዋዋሪ መምህርነት በጉድኝት ማዕከላትና ከተቻለም በየትምህርት ቤቱ እንዲሰሩ በመመደብ አተገባበሩን መከታተል
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያዎችንና ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎችን በመመደብ አተገባበሩን መከታተል መንገድ ማመቻቸት

## የአጠ/ትም/ሱፐ/የተቋ/ ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት

- የአካቶ ትምህርት አቀራረብ በሁሉም የትምህርት ፕሮግራሞች ማለትም በቅድመ መደበኛ፤ በመጀመሪያ ደረጃ፤ በሁለተኛ ደረጃ፤ ትምህርቱ ስለመካተቱትን በቼክሊስት የታገዘ ድጋፍና ክትትል ማድረግ

# የስርዓተ ጾታ የስራ ክፍል ዳይሬክቶሬት

- የአካል ጉዳተኛ ሴት ተማሪዎችን ተሳትፎን በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ለማሳደግ አሁን እየተሰራበት ያለውን አዎንታዊ ድጋፍ (affirmative action) ተግባራዊ ማድረግ፤
- በክልሉ በሚካሄዱ ሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ውስጥ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን በተለይም የሴት አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሻሻል የተለያዩ መንገዶችን በመቀየስ ተግባራዊ ማድረግ ለአብነትም ተጨማሪ ትምህርት መስጠት (tutorial) የኪስ ገንዘብ መስጠት፤ የንፅህና መጠበቂያ፤ የመማሪያ ቁሳቁሶችን ና ሌሎችንም መስጠት

- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርትን ተግባራት በበጀት ተደግፎ እንዲተገበር በክልሉ ለመተግበር ማቀድ፤
- የህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2009 በተግባር ላይ መዋሉንና የት/ቤት ህንፃዎች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበር ላይ ድርሻ ካላቸው የተለያዩ አጋሮች ጠንካራ አጋርነት መፍጠር
- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ አተገባበርን ለማጠናከር ተጨማሪ ፈንድ ከለጋሾች ማፈላለግ

## የአጠቃላይ ትምህርት እንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት

- ት/ቤቶች በስታንደርዱ መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን

ተጠቃሚ ማድረጋቸውን በማረጋገጥ የደረጃ ፍረጃ ያደርጋል

## የመረጃ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት

- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች መረጃ ያታን መሰረት በማድረግ ለመሰብሰብ ስርዓት መዘርጋትና ትምህርት ሚኒስቴር ለመረጃ መሰብሰቢያ ከተዘጋጁት መሳሪዎች ጋር በማጣጣም መረጃውን ከትምህርት ቤቶች ደረጃ ጀምሮ እንዲሰበሰብ ማድረግ
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች መረጃን በጉዳት አይነትና ደረጃ ተለይቶ እንዲሰበሰብ በማድረግ በማደራጀት በመተንተን በስራ ላይ እንዲውል ማድረግና ለሚመለከታቸው መላክ

## የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዬች ዳይሬክቶሬት

- በአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የትምህርት መብት ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የተለያዩ የግንዛቤ መስጨበጫ መልዕክቶችንና ማስታወቂያዎችን የተለያዩ ሚዲያዎችንና ቀስቃሽ ፅሁፎችን በመጠቀም ማስተላለፍ
- በልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራትን በቢሮዎ በሚዘጋጁ በራሪ ወረቀቶች፣ መፅሄቶችና ሌላ የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊቢሮው ማህበረሰብና ለሚመለከታቸው አካላት ማስተላለፍ የግንዛቤ ማሰደግ ስራን ማከናወን።

**Thank you for your attention**